# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## <u>ሰንደቅ ዓላማችን ሲጠቃ፥ ኢትዮጵያዊ ክብራችን ይነካል!</u>

ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተገነጠለችበት አሥራ-አምስተኛ ዓመት በአሥመራ ከተማ በተከበረበት ወቅት የሸዓብያ መሪዎች፥ ሌሎች የተጋበዙ እንግዶችና የከተማው ሕዝብ በተገኙበት አደባባይ ላይ ከቀረቡት ትዕይንቶች አንዱ የኢትዮጵያን ሰንደቅ-ዓላማ መሬት ላይ ጥሎ እንደ አልባሌ ነገር መርገጥ እንደነበረ ተስተውሏል። ይኸንን አስፀያፊ ድርጊት የተመለከቱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅግ የተቆጡ መሆናቸው ከያለበት እየታየ ነው። የሸዓብያ መሪዎች በተለይ በቅርቡ በዩትሬክት ሆላንድ ላይ የተቋቋመውን "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ" የተባለ ስብስብ በመደገፍ "ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆመናል" እያሉ በሚለፍፉበት በአሁኑ ወቅት ይኸንን ዓይነት አግባብነት የሌለው የንቀት ድርጊት እንዲፈጸም ፈቅደዋል የሚለውን ነገር ለማመን ያቃታቸው ሌሎች ኢትዮጵያውያን ደግሞ "ድርጊቱ አልተፈጸመም፥ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች የተንኮልና የፈጠራ ፕሮፖጋንዳ ነው" ሲሉ እየተደመጡ ነው። በእርግጥም እንደዚህ ከሆነ በሁኔታው በጣም ለአዘነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሸዓብያ መሪዎች በኩል የማስተባበያ መግለጫ መውጣት ነበረበት። ይኸ አለመደረጉ ስህተት ነው። ድርጊቱ ተፈጽሞ እንደሆነ ደግሞ እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ብቻ ሳንሆን አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ወገን ሁሉ ከሕዝባችን ጎን ቆመን የምናወግዘውና የምንዋጋው የጥላቻና የንቀት አካሄድ ነው።

ደግሞ ተደጋግሞ እንደተነገረውና እኛም በሙሉ ልብ እንደምናምንበት ጥቂት ገዥዎች እንዳመቻቸው ከሚቆሰቁሱት ግጭት በስተቀር ወንድማማች በሆኑት የኤርትራና የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ መኻል ምንም ዓይነት ጠላትነት የለም። ነገ በሁለቱም በኩል ዴሞክራሲና እርቅ ሰፍኖ በእርግጥ ሕዝብ የራሱ ዕድል ወሳኝ የሚሆንበት ሥርዓት ሲፈጠር ይኸ የወንድማማችነት መንፈስ ጎልብቶ፥ የተሻለ መከባበርና መቀራረብ ተፈጥሮ፥ አንድነታቸውን አጠንክረውና እጅ ለእጅ ተያይዘው አዲስ የሰላምና የብልጽግና ምእራፍ እንደሚከፍቱ ለአፍታም ቢሆን አንጠራጠርም። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ የአንድ ሕዝብ የታሪኩ፥ የጎልውናው፥ የኩራቱና የወደፊት ተስፋው ምልክት በሆነና <u>ከትውልድ ትውልድ የደም ዋጋ እየተገበረበት</u> ዘመናትን በአስቆጠረ <u>ክቡር ዓርማ</u> ላይ እንዲህ ዓይነቱ የጥላቻና የንቀት እርምጃ ምን ያህል አግባብ የሌለው አድራጎት ቢሆን ለዘመናት የቆየውንና ከጥቂት ገዥዎች ዘልቆ ገና ለዘመናት የሚቀጥለውን የአንድነትና የወንድማማችነት መንፈስ ቅንጣት የሚቀይረው አይሆንም። ይኸንን ካልን ዘንዳ ለሸዓብያ መሪዎችም ሆነ ይኸንን የለየለት የሕዝብ ንቀትና የጥላቻ እርምጃ በቸልታ ለማየት ለሚቃጣቸው አንዳንድ ወገኖች ሁለት ነጥቦችን ማስቀመጥ እንወዳለን።

አንደኛ ይኸ ሰንደቅ ዓላማችን የእሩቁን ትተን ከአድዋ እስከ ማይጨው፥ በአምስት ዓመታት የፋሽስት ወረራ ዘመንም በአገራችን ደኖችና ሸንተረሮች የኢትዮጵያና ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የኤርትራ አርበኞች <u>"እናት ኢትዮጵያ ወይም ሞት" እያሉ ደማቸውን ያፈሰሱለትና በደማቸው ያስከበሩት ክቡር ዓርማና የጎልውናችንና የነፃነታችን ምልክት</u> እንደሆነ የሸዓብያ መሪዎች ጠንቅቀው ሊያውቁት ይገባል እንላለን። በአስከፊው የጣልያን ዘረኛ ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ ኤርትራውያን በየክብረ በዓሉ፥ በየሰርጉና ድግሱ፥ በደስታውም በሃዘኑም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የማንነታቸውና የነፃነት ፍላጎታቸው መግለጫ አድርገው ያከብሯት እንደነበር፥ ይኸ በአደባባይ ከመገለፅ ሲከለከል ደግሞ በየጓዳው ባሉ እቃወቻቸው ተጠምጥሞ በፍቅር፥ በክብርና በአለኝታነት ይቀመጥ እንደነበር ይታወቃል።


| | | |
|---|---|---|
| ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office) | ኢትዮጵያ (Ethiopia) | አውሮጳ (Europe) |
| ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246 | ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box | Jonathan Str. 82 |
| Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A | Addis Abeba,Ethiopia | 2524 JJ The Hague, |
| ስልክ/Tel.: 202-291-4217; | ስልክ/(Tel.) 251_______ | Netherlands |
| ፋክስ/Fax: 202-291-7645 | ፋክስ/Fax:2511________ | Tel/Fax 31 70 394 6132 |

ይኸ አረንጓዴ÷ ብጫ÷ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ከእኛም አልፎ አገራችን በልጆቿ ከባድና ክቡር መስዋዕትነት ብቸኛ የክብር ፋና በነበረችበት የቅኝ ግዛት ዘመን በጭቆና ቀንበር ሥር ለነበሩትና በተለይም ለመላው ጥቁር ዓለም ብቸኛ የተስፋ÷ የነፃትነትና የአርነት ትግል መሰባሰቢያ አርማ እንደነበር እናስታውሳቸዋለን፡፡ ከዚህም ዘልቀን ለአፍሪቃ ሕዝቦች የነፃነት ጎኅ እየቀደደ ሲሄድ ከማሊ እስከ ጋና÷ ከሴኔጋል እስከ ካሜሩን ወደ አሥራ-አምስት የሚጠጉ የአፍሪቃ አገሮች ይኸንን ሰንደቅ ዓላማችንን በተለያየ አቀማመጥና ቅርጽ የራሳቸው ሰንደቅ-ዓላማ አድርገው በአገራዊ የሉአላዊነት ምልክትነት በክብርና በኩራት እንደሚያውለበልቡት እንጠቅስላቸዋለን፡፡ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ይኸንን ክቡር የሆነ የአገራዊ ኅልውናችንና የብሔራዊ ኩራታችን ምልክት ተራ "ጨርቅ" ብለው እንዳጣጣሉት የሸዓብያ መሪዎችም እንደእኛ ያውቁታልና እነሱ እንዲህ ዓይነት ድርጊት በአደባባይ ሲፈጽሙ ይኸንን ድርጊታቸውን "በፀረ-ወያኔነት" ሊያሳብቡት ከቶውንም አይችሉም፡፡ ይኸ የለየለት ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ኢትዮጵያዊነት የጠላትነት ድርጊት ነው፡፡

ትላንት የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎችን ፀረ-ሰንደቅ ዓላማ ቅስቀሳ በኢትዮጵያዊነታችን ዓይን ላይ እንደመጣ ፀረ-ኢትዮጵያ ቅስቀሳ ቆጥረን እንደተቃወምነውና እንደተዋጋነው ሁሉ ዛሬም የሸዓብያ መሪዎች ወያኔ ላይ ያነጣጠሩ መስለው በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የቃጡትን ስድብ÷ ብሔራዊ ውርደትና ንቀት እንደምንቃወመውና እንደምንዋጋው በግልፅ መታወቅ ይኖርበርታል፡፡ ሌሎች የአገራችን ዴሞክራቶችና አገር-ወዳዶችም ይኸንን ያልተጠበቀ ክብረ-ነክ የጥቃት ድርጊት ያለ አንዳች ማወላወል በሙሉ ድምፅ ማውገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጀግናው ዘርአይ ደረስ በጣሊያን አደባባይ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠው ለዚች የወያኔ አጉራ ዘለል መሪዎች ተራ ጨርቅ ላሏትና አሁን በአሥመራ ለተዋረደች ብሔራዊ ምልክታችን ክብር እንደነበር ከቶውንም ሊዘነጋ አይችልም፡፡

ሁለተኛም ይኸንን እርምጃ እንደቀላል "ፀረ-ወያኔ" እርምጃ አድርገው ለማቅረብ ለሚግደረደሩ ሁሉ ሌላም ግልፅ መልእክት ለማስተላለፍ እንወዳለን፡፡ ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች የተያያዝነው ታሪካዊ ተጋድሎ በፀረ-ወያኔ/ኢሕአዴግነት የሚወሰን ተራ ግርግር አይደለም፡፡ ከዚያ አልፎና ዘልቆ ለኢትዮጵያ ክብር÷ ለሕዝቧ እኩልነት÷ አንድነትና ወንድማማችነት የሚደረግ ጥልቅና የሩቁን ያየ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ የተቀደሰ ዓላማ÷ ሰፊና ታሪካዊ መራር ትንንቅ ነው፡፡ ኅብረታችን በቅርቡ "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ" የተባለና የሸዓብያ መሪዎችም የሚደግፉት ስብስብ በዩትሬክት ከተማ ሲመሠረት የስብስቡ  ስም ኢትዮጵያ የሚለው ቃል እንዲጨመርበት የጠየቀበትም ዋናው ምክንያት በመንግሥት ደረጃ በጀት ተይዞለት ጦርነት የተከፈተበት የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከእያንዳንዱ የጋራ ትግል እርምጃ ጋር አብሮ እየጎለበተ እንዲሄድ በማሰብ ነበር፡፡ አሁንም ከዚህ የተለየ አቋምም ሆነ የምንለው ነገር የለንም፡፡ የሸዓብያ መሪዎች "በፀረ-ወያኔው" ትግል ከጎናችሁ ነን እያሉ እዚያው በዚያው ደግሞ የወያኔ/ኢሕአዴግነት ሳይሆን የኢትዮጵያዊነት ማንነትና ምንነት መታወቂያ መግለጫና የክብር ምልክት የሆነው አረንጓዴ÷ ብጫ÷ ቀይ ሰንደቅ ዓላችንን በአደባባይ እንደቆሻሻ ጨርቅ ሲረጋግጡ ልናስተላልፍላቸው የምንሻው መልእክት በጣም ግልፅ ነው፡፡ እኛም ሆንን መላው ሕዝባችን የምናካሂደው ትግል ከአላፊ ጠፊዎቹ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች መውደቅ ባሻገር በዚህ ከየአቅጣጫው የፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ጥቃት በሚሰነዘርበት ሰንደቅ-ዓላማችን ዙሪያ እንደገና በእግሯ የምትቆም ኩሩ አገር እውን ለማድረግ የሚደረግ ትግል ነው፡፡ በመሆኑም ይኸ "ፀረ-ወያኔ" እርምጃ ለኢትዮጵያችንና የእሷነት መግለጫና ምልክት ለሆነው ለዚህ ጥቃት ለደረሰበት ሰንደቅ ዓላማችንም እንደሆነ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

ሞት ለኢትዮጵያ ጠላቶች!
ሰንደቅ ዓላማችን የብሔራዊ ክብራችን ምልክት ናት!!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም